# እንደ ሸሚዝ የሚቀያየር የፖለቲካ እምነትና አቋም

## ክፍል ሁለት (ካለፈው የቀጠለ)

በሸዋይልማ ኪዳኔ (ጀርመን)

አንድ ፖለቲከኛ የአባላቱንና የደጋፊዎቹን ከዚያም አልፎ የፖለቲካ ተቃዋሚዎቹን ከበሬታና አድናቆት ማግኘት የሚችለው ለፖለቲካ እምነቱ በቆራጥነት ያለማወላወል ሲታገል እንደሆነ መናገሩ መድገም ካልሆነብኝ በስተቀር አዲስ ነገር እንዳልሆነ በሚገባ እገነዘባለሁ። ፖለቲካም ተለዋዋጭ ክስተት እንደመሆኑ የፖለቲካ እምነትም ሊለውጥ እንደሚችልም ጠንቅቆ ይገባኛል።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ግን የፖለቲካ እምነታቸውን እንደፈለጉ ለመቀየር የማይቸግራቸው፣ አቋማቸውን በሌላው ላይ ለመጫን የማይፈሩ፣ የፖለቲካ ድርጅትን ዝቅ አድርጎ እንደ ግልንብረትነት ለማየት የሚፈልጉ ፖለቲከኞችን የሚመለከት ነው። እንደነዚህ ዓይነቱ ፖለቲከኞች ፖለቲካን ቲያትር ያስመስሉታል። ጥያቄው ፖለቲከኞቻችንን ምን ያህል እናውቃችዋለን? የሚል ነው። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ይህን ጥያቄ ለመመልስ አንድን ፖለቲክኛ በምሳሌነት እንዲያቀርብ ይገደዳል። አስገራሚ የሆነ የአቋም መለዋውጥ ከሚታይባቸው "በተቃዋሚ የፖለቲካ ጎራ" ውስጥ ከሚገኙ ፖለቲከኞች ውስጥ ከመድኅን ፓርቲ አንጃ በመፍጠር የተገለሉት ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በአሁኑ ስዓት በዋነኛነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ታጠቅ ሰንቅ

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት ከስልጣን ለማውረድ ከትጥቅ ትግል ውጭ አማራጭ የሌለ መሆኑን በማመን በ1985 ዓ.ም በካሴት ተቀርጾ ለኢትዮጵያ ሕዝብና በተለይም ለኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ በተበተነው መልዕክታቸው ውስጥ ስለ ትጥቅ ትግል አስፈላጊነት ሲናገሩ፦

> *" ... ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ... ለወቅቱ የበሰለ ፀር ወያኔ ይዞታ ተስማሚ የሆነው ትግል የትጥቅ ትግል ነው። በኃይል ብቻ ስልጣን ላይ የቆየ አካል በኃይል ካልሆነ በስተቀር በራሱ ፍላጎት፣ በፖለቲካና በዲፕሎማሲ ትግል ብቻ ከስልጣን ይወገዳል ብሎ ማመን የዋህነት ነው። ... የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ትግል፣ ሰላማዊ ሰልፎችና ትዕይንተ ሕዝቦች፣ ንግግሮችና ፕሮፓጋንዳዎች በኃይል ካልተደገፉና ካልታጀቡ በስተቀር ፋይዳ የሌላቸው መሆኑን ግንዛቤ አግኝቶ የትጥቅ ትግሉን መጀመር ብቻ ሳይሆን መጧጧፍ ይኖርበታል። ... "*

የኮ/ል ጎሹ ወልዴ የክተት ጥሪ ለኢትዮጵያ ሕዝብ 1985 ዓ.ም

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በትጥቅ ትግሉ አቋማቸው በመግፋት በወቅቱም የመድኅን ፓርቲ ሊቀመንበር የነበሩ በመሆኑ አጋጣሚውን በመጠቀም ይህን የግል እምነትና አመለካከት በመድኅን ላይ በመጫን የድርጅቱ ፖሊሲ እንዲሆን ማድረግ በመቻላቸው ፓርቲው የትጥቅ ትግሉን ከፖለቲካና ዲፕሎማሲያዊ ትግሉ ጎን ለጎን እንደሚያካሂድ ይፋ አደረገ። ኮ/ሉ በፓርቲው ሊቀመንበርነታቸው በየቃለ ምልልሱ ላይ ስለ ትጥቅ ትግሉ አስፈላጊነት ማስረዳቱን ተያያዙት። ኢትዮጵያን ሬጅስተር በመባል ከሚታወቀው በእንግሊዘኛና በአማርኛ ቋንቋዎች እየታተመ ከሚወጣው መጽሔት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ላይ የትጥቅ ትግሉን አስመልክቶ ሲያብራሩ፦

> " ... Ours is a low-intensity and geographically limited defensiv military opertions against an aggressive over-equipped and very large occupying army that terrorising the Ethiopian people. ... Our second objective is to aplly maximum military pressure on TPLF/EPRDF leadership in order to force it to make substantial concessions at a conference table. ... To this effect our defensive military units have recently freed poletical prisoners from Debre Brehan and elsewhere in the Country ... "

Goshu Welde
ETR. , September 1994

የወያኔ መንግስትና የተቃዋሚ ኃይሎችን ለማቀራረብ ይቻል ዘንድ በአሜሪካን መንግስት ተቋቁሞ የነበረውን ግብረ ኃይል (The Task Force on Ethiopia) የመሩትና የኮንግሬስ አባል የነበሩት ሚ/ር ሃሪ ጆንስተን በወቅቱ የመድኅን ሊቀመንበር ለነበሩት ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በጻፉት ደብዳቤ ላይ የትጥቅ ትግሉን በሚመለከት ሲናገሩ፦

> " --- we are particularly disturbed by your call for an armed struggle from exile. The Ethiopian people have sufferd for too long because of political leaders whose primary interest is to assure power by any means necessary. ... "

Harry Johnsten, M.C
January 17, 1995

ብለዋቸው ነበር።

የወያኔውም መሪ አቶ መለስ ዜናዊም የኮ/ል ጎሹን የክተት ጥሪ በተመለከተ በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ እያሾፉ አንድ ጊዜ “ኮ/ል ጎሹ ከዋሽንግተን ዲሲ ሆኖ በርቀት መቆጣጠሪያ ይወጋናል ብለን አናስብም” በሌላ ጊዜ ደግሞ “በሚገባቸው ቋንቋ እናነጋግራቸዋለን” እያሉ የኮ/ል ጎሹን የትጥቅ ትግል አስመልክቶ እየደጋገሙ በንቀት ተናግረው ነበር። በዚህም ብቻ ሳያበቃ መለስ ዜናዊ አንድ ጊዜ በደቡብ ኢትዮጵያ ጉብኝት ላይ በነበሩበት ጊዜ ንግግር ሲያደርጉ የኮ/ሉን የትጥቅ ትግል እያጣጣሉ የሚከተለውን ብሎ ነበር።

> *“ … ይለፍልፉ። ሰው በህልሙ አይጓዝም አይባልም። እነ ጎሹ በናንተ ልጆች እንጂ የተዋጉት በራሳቸውማ ፈሪዎች ናቸው። ቀረብ ሲሏቸው ሩጫ ብቻ። “*

መለሰ ዜናዊ
በ1986 ዓ.ም የደቡብ ኢትዮጵያን ክልል ሲጎበኝ ካሰማው ንግግር

ትላንት ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ስለትጥቅ ትግል አስፈላጊነት ሲሰብኩ እንዳልነበር ዛሬ ደግሞ ዞር ብለው ጆሮሃችንን እስኪደክመው ድረስ ስለሰላም ትግል አስፈላጊነት ሲያስተምሩን ትላንት በወያኔ ላይ ሲያዘምቱት ስለነበረው ሰራዊታቸው ግን ትንፍሽ አይሉም። ይልቁንስ መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያና “የፓርቲያቸው” ጠላት እንዳልሆኑና መጠላት የሌለባቸው ሰው ስለመሆናቸው እዚህ ጀርመን ድረስ መጥተው ነግረውን ወደመጡበት ወደ አሜሪካ ተመለሱ። ይህን ለማለት ያበቃቸው መለስ ዜናዊ ምን ቢሏቸው ይሆን ብሎ ግን የተዬቃቸው የለም።

## <u>የሰላም አርበኛ</u>

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ትላንት የወያኔ/ኢ.ህአዴግ መንግስትን ከስልጣን ለማስወገድ ከትጥቅ ትግል ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌለ ነጋጠባ ሲሰብኩ እንዳልነበር ዛሬ ወያኔ/ኢ.ህአዴግ በሰላማዊ ትግል ከስልጣኑ እንዳስወግደው ይፈቀድልኝ ብለው ለወያኔ/ኢ.ህአዴግ መንግስት የምርጫ ቦርድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ ጽ/ቤት ማመልከቻ አቀረቡ። የቀድሞ የትግል አጋሮቻቸው የነበሩትን ኢትዮጵያውያኖች በጠረኝነት በመክሰስ ስለ ሰላማዊ ትግል አስፈላጊነት እየዞሩ ትምህርት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። የኢትዮጵያዊነት ድምፅ ተብሎ ከሚጠራው አንድ በዋሽንግተን ከተማ ከሚገን የሬዲዮ ጣቢያ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ላይ የትጥቅ ትግል በኢትዮጵያ ውስጥ ለምን ሊሰራ እንደማይችል ሲያስረዱ፦

> *“ የጦርነት መንገድ የማያዋጣ ነው። … ዓለማችን በሁለት ጎራ በተከፈለችበት ወቅት የትጥቅ ትግል ማድረግ ይቻል ነበር። ወደ ሶቪዬት ህብረት፣ ቻይና ወይም ኩባ ሂዶም የመሳሪያ ዕርዳታ ማካበት ይቻል ነበር። አሁን ግን ዓለም በአንድ ልዕለ ኃይል መዳፍ ስር ስለሆነች የትጥቅ ትግል አያዋጣም። … “*

ቃለ ምልልስ ከኮ/ል ጎሹ ወልዴ ጋር
የኢትዮጵያዊነት ድምፅ ነሐሴ 4 ቀ 1995 ዓ.ም

ዓለማችን ወደ አንድ ልዕለ ኃይል መንግስት መዳፍ የተሸጋገረችው ዛሬ ሳይሆን የቀድሞዋ ሶቪዬት ህብረት በ1983 ዓ.ም ከፈራረሰች በኋላ መሆኑን ዘንግተው ከሆነ እጅግ በጣም የሚያሳዝንና የሚያስገርም ጉዳይ ነው። ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በ1985 ዓ.ም ወያኔን ከስልጣን ለማስወገድ ከትጥቅ ትግል ውጭ አማራጭ የለም ብለው የክተት ጥሪውን ሲያስተላልፉ ዓለማችን ልክ እንደዛሬው በአንድ ልዕለ ኃይል መንግስት ስር ወድቃ እንደነበረች አጥተው ሳይሆን ማስተባበያ ምክንያት ከማጣት የመነጨ ነው ብሎ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ያምናል። ሆኖም ግን ኮ/ል ጎሹ ዓለማችን በአንድ ልዕለ ኃይል መንግስት ከወደቀች በኋላ ትናንት በዲሞክራቲክ ኮንጎ (የቀድሞዋ ዛየር) ውስጥ ዛሬ ደግሞ በላይቤሪያ ውስጥ የመንግስት ተቃዋሚ ኃይሎች ባካሄዱት የትጥቅ ትግል መንግስት እንዴት ሊለውጥ እንደቻለ ቢጠየቁ  ምን መልስ ይሰጡ እንደነበር መስማት ብንችል መልካም ነበር።

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ዛሬ ከማንም በላይ በመድኅን አመራርን ላይ እና በተለይም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረትን (ኢ.ዴኃህ) የፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊ (Treasry Official) እና የመድኅን ፓርቲ ሊቀመንበር የሆኑትን ፕ/ር ስዩም ገላዬን በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ በጠረኝነት መክሰስ ስራዬ ብለው ተያይዘውታል። ስለ ሰላም ትግል በሚሰብከው መግለጫቸው ውስጥ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ እስከ የካቲት 19 ቀን 1995 ዓ.ም ድረስ የስራ አስኪያጅ ኮሚቴና የምክር ቤቱ አባል ሆነው ሲያገለግሉበት የነበረውን የመድኅን ፓርቲን አመራር በሚያጣጥለው መግለጫቸው ውስጥ የትጥቅ ትግልን በሚመለከት የሚከተለውን ያስነብቡናል።

> *“ … እንደ ተውዘግዛጊ ሚሳይል በ10000 ኪ/ሜትር ርቀት ላይ ሆነን ወያኔን ለማስወገድና ስልጣኑን ለህዝብ ለመመለስ አይቻልም። … የተሳካ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ዕቅድ ይጠይቃል። … ያለ ጥናት፣ ያለ ዕቅድ፣ ያለ ዝግጅትና ያለ ሠራዊት ከሩቅ ሆኖ ዉጤታማ ጦርነት ማካሄድ ይቻላል? … “*

የኮ/ል ጎሹ ወልዴ መግለጫ
ማርች 7 ቀን 2003

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ የክተት ጥሪውን ሲያውጁ ያለ ጥናት፣ ያለ ዕቅድ፣ ያለ ዝግጅትና ያለ ሠራዊት … ከነበረ "ሪሞት ኮንትሮል" የሚለው የአቶ መለስ አባባል እንከን አይወጣለትም። የኮ/ል ጎሹ ወልዴ የሰላም አርበኝነት የስምንት ወር እድሜ ያስቆጠር ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ ከባዶ ቀርነት አልፎ ነፍስ ዘርቶ በዓይን የሚታይ የሰላም ትግል መሆን አልቻለም። እኔ በግሌ የክ/ሉን የሰላም አርበኝነት ቀን አንድ ብዬ መቁጠር የምጀምረው ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ቃላቸውን ጠብቀው አገር ቤት ገብተው በህዝቡ መሀል በመንቀሳቀስ በዓይን የሚታይ ፖለቲካ ማካሄድ ሲጀምሩ ብቻ ይሆናል። ከዚህ ውጭ ሌላው ሁሉ ባዶ ቃልና ጩኸት ብቻ ነው።

## የድርሻዎን ያንሱ

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ከኦክቶበር 19 ቀን 2002 ጀምሮ በስውር፤ ከማርች 7 ቀን 2003 ጀምሮኦ ደግሞ በግልጽ በአደባባይ በጦረኝነት የሚከሱት የመድኅን ፓርቲ አመራር ውስጥ ከድርጅቱ እስከ ተገለሉበት እስከ የካቲት 19 ቀን 1985 ዓ.ም ድረስ በፓርቲው የአመራር አካል ወስጥ በአባልነት ሲያገለግሉ እንደነበር የሚታወቅ ነው። እንበልና መድኅን በጦርኝነት ቢከሰስ ኮ/ሉ ከክስ ነፃ ሲሆኑ አይታየኝም። ፓርቲውን በሊቀመንበርነት በመሩባቸው የመጀመሪያዎቹ አራት ዓመታት ውስጥ ለተካሄደው የትጥቅ ትግል ከማንኛውም አባል በላይ ተጠያቂው ኮ/ል ጎሹ ስለመሆናቸው ያወጧቸውና ለህዝብ ይበተኗቸው የነበሩት ወታደራዊ መግለጫዎች ምስክሮች ናቸው።እስኪ አንዳንዶቹን አብረን እንመልከት።

በኮ/ል ጎሹ ወልዴ አመራር ሰጭነት በተካሄደው የትጥቅ ትግል በኢትዮጵያ መድኅን ሠራዊት (ኢመሠ) የቆሰሉ የወያኔ ወታደሮችን፣ በንብረት ላይ የደረሰውን ጉዳትና የተማረኩ የጦር መሳሪያዎችን ቁጥር ሳላስገባ በትጥቅ ትግሉ የተገደሉ የወያኔ ወታደሮች፣ ፖሊስና የደኅንነት አባላትና ከእስር ቤት ኢመሠ ያስለቀቃቸውን የፖለቲካ እስረኞች ብቻ ኮ/ሉ ካወጧቸው ጥቂት ወታደራዊ መግለጫዎች ላይ አብረን እናንብብ። በዚህ አጋጣሚ ሳላነሳ ማለፍ የማልፈልገው ኢመሠ የትጥቅ ትግሉን ያካሄደውና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ድሎች በአምባገነኑ የወያኔ መንግስት ሠራዊት ላይ የተቀዳጀው ዓለማችን በአንድ ልዕለ ኃይል መንግስት ስር ከወደቀች በኋላ መሆኑን ጭምር ነው።

ግንቦት 3 ቀን 1986 ዓ.ም በወጣው ወታደራዊ መግለጫ መሰረት በኢመሠ 5 የወያኔ ወታደሮች ሲገደሉ፣ 151 የፖለቲካ እስረኞችን ከደብረብርሃን እስር ቤት ሲያስለቅቅ፤ ግንቦት 15 ቀን 1986 ዓ.ም 11 የወያኔ ወታደሮች፣ ሐምሌ 18 ቀን 1986 ዓ.ም 7 ወታደሮች፣ ነሐሴ 15 ቀን 1986 ዓ.ም 17 ወታደሮች፣ ጥቅምት 3 ቀን 1987 ዓ.ም 12 ወታደሮች፣ ጥቅምት 16 ቀን 1987 ዓ.ም 9 ወታደሮች፣ ጥር 16 ቀን 1987 ዓ.ም 3 የወያኔ ፖሊሶችና አንዲት የወያኔ ሰላይ ስትገደል በጠቅላላው 61 የወያኔ ወታደሮች፣ ሶስት ፖሊሶችና አንዲት የድኅንነት አባል ላይ ኢመሠ ጉዳት ማድረሱን በወቅቱ ባወጧቸው ወታደራዊ መግለጫዎች ለህዝብ አስታውቀዋል። በተጨማሪም 151 እስረኞችን ከደብረብርሃን እስር ቤት ስለማስፈታታቸው የብስራት ሬዲዮና የአዲስ አበባው የኢህአዴግ ሬዲዮ ጣቢያ አገልግሎት ዜና ሀቀኛ መሆኑን አምነው በግንቦት 3 ቀን 1986 ዓ.ም ባወጡት ወታደራዊ መግለጫ ላይ ኀላፊነቱን በመቀበል አረጋግጠዋል።

የመድኅን አባላት በሙሉና ብዙ ኢትዮጵያዊያኖች ጠንቅቀው እንድሚያውቁት የወያኔ/ኢህአዴግ የሽግግር መንግስት ዐቃቤ ሕግ በመድህን ላይ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ሀ/አ እና 252/1/ሀ የተጠቀሰውን በመተላለፍ በኢትዮጵያ ውስጥ ጦርነት እንዲነሳ በማድረግ በሚል በታህሳሱ 1986 ዓ.ም የአዲስ አበባው የሰላምና የእርቅ ጉባዔ እንዲሳተፉ በመድኅን ተወክለው በጉባዔው እንዲገኙ የተወከሉትና በወቅቱ በመድኅን የሥ/አ/ኮሚቴ አባል የነበሩት ግለሰብ ላይ በማዕከላዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከፈተ ክስ ነበር። ዐቃቤ ሕጉ ግለሰቡን ሲከስ ካልተያዙ ግብረአበሮቹ ጋር በማለት በቁጥር አንድ ላይ ኮ/ል ጎሹ ወልዴን በመጥቀስ በሽግግር መንግስቱ ላይ የትጥቅ ትግል በማካሄድ በሚል በሌሉበት አብረው ተከሰው እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም። ሁላችንም እንደምናውቀው በዚያን ግዜ በሽግግር መንግስት ላይ የነበረው የአቶ መለስ መንግስት ዛሬም ስልጣኑን በመሳሪያ ኃይል በማስጠበቅ የኢትዮጵያን ህዝብ ረግጦ እየገዛ ነው። ኮ/ል ጎሹ የመድህንን አመራር በጦረኝነት ሲከሱ መገንዘብ የሚገባቸው ቁምነገር ቢኖር በእሳቸው ሊቀመንበርነትና አመራር ሰጭነት በኢመሠ ስለተካሄደው የትጥቅ ትግል ኃላፊነቱን መውሰድ ያለባቸው እሳቸው እራሳቸው መሆኑን ነው። ይህ ሳይሆን ግን ኮ/ል ጎሹ ወልዴ የጥፋት ጣታቸውን በመድህን አመራር ላይ ብቻ የሚቀስሩ ከሆነ ግን ሶስት የታጠፉ የእጅ ጣቶቻቸው ወደ እሳቸው ማመልከታቸውን ፈጽሞ አልተገነዘቡም ማለት ነው። የቀረውን ክስ ከእሳቸው በኋላ የመድኅንን አመራር ለተረከቡት የድርጅቱ አባላትና ፍርዱንም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቢተውለት መልካም ይመስለኛል ። ኮ/ሉ ይህን እንደሚያደርጉ ሙሉ እምነት አለኝ።

## ኤርትራ - የፖለቲካ ጆከር

ስለ መድኅን የፖለቲካና ዲፕሎማሲ ትግል ሲነሳ ሳይጠቀስ ሊታለፍ የማይችል ጉዳይ ቢኖር ፓርቲው በወያኔ ተባባሪነት የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን ሽፋን በመጠቀም በኤርትራ የተካሄደውን "ሬፈረንደም" በተመለከተ መድኅን ያደረገውን ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ዘመቻ ነው። መድኅን ያካሄደው የዲፕሎማሲ ዘመቻ የአፋር፣ የኩናማን የሻዋ ተወላጅ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ዜጎች ያለፍላጎታቸው የዜግነት መብታቸው ተደፍሮ

በሻዕቢያ ሥር እንዲተዳደሩ መገደዳቸውን በመቃወም ሲሆን የኤርትራን መገንጠል ማቆም ባይቻልም ዛሬ በአገራችን ውስጥ ለኢትዮጵያ የግዛት ሉዓላዊነትና ብሔራዊ ጥቅም ቅንጣት ያህል የማይቆረቆር መንግስት ስልጣን በያዘበት ሰዓት መድኅን በዲፕሎማሲ ትግሉ በተባበሩት መንግስታት ድርጅትና በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሲታወስ የሚኖር አስተዋጽኦ ማድረግ ችሏል። ለዚህም በማስረጃነት ኮ/ል ጎሹ የመድኅን ሊቀመንበር በነበሩበት ጊዜ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፃፏቸውን ደብዳቤዎችና የወቅቱ የፓርቲው ሊቀመንበር ፕ/ሮ ስዩም ገላዬ ለተባበሩት መንግስታት ማህበር ዋና ፀሐፊ ለሚ/ር ኮፊ አናን በጀንዋሪ 21 ቀን 2002 የፃፉትን ደብዳቤ መመልከት ብቻ በራሱ በቂ ይመስለኛል። ምናልባትም ማጋነን ባይሆንብኝ መድኅንን በመድኅንነቱ እንዲታወቅ ካደርጉት የትግል ዘርፎች ውስጥ ግንባር ቀደሙ የኤርትራ ጉዳይ ነው ለማለት ይቻላል።

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ በወቅቱ የተባበሩት መንግስት ዋና ፀሐፊ ለነበሩት ለዶ/ር ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ በጻፉት ደብዳቤ ውስጥ በኤርትራ ሊካሄድ የታሰበውን "ሬፈረንደም" ህገወጥነት ሲገልጹ፤

> " ... The fraudulent nature of the process, its outcome as well as the indecent haste with which the referendum resolution is being rushed through the UN will immediately rekindle the flame of liberation amongst the people of Afar and others who will legitimiately Concluded that EPLF and the UN have colluded in denying them their inalienable right to self-determination. ... History and the Ethiopian people will never forget and will never forgive what the UN and freacherous leadership in Addis Ababa and Asmara are doing to Ethiopia. ..."

Goshu Wolde
Chairman
MEDHIN, Oct. 30, 1992

በተጨማሪም ኤርትራ ፈጽሞ የአሰብን ክልል የማይጨምርና የክልሉ ነዋሪ የሆነው የአፋር ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ለመኖር ፍላጎት ያለውና በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምን መሆኑን ከኢትዮጵያን ሪቪው ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ላይ፦

> " ... The territory of Eritrea does not include the stripland along the Red Sea down to Djibuti which has been inhabited by and historically and culturally associated with the people of Afar who had, for centeries enjoyd autonomous association with Ethiopia. ... The people and their leadership have also repeatedly expressed their wish and determination to live in autonomus association with Ethiopia. ... "

Goshu Wolde
Ethiopian Reiview, Nov. 1992

ሆኖም ግን ኮ/ል ጎሹ ወልዴ መድኅን በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ በጁን 17 ቀን 2001 ዓ.ም በጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ የኤርትራን ጉዳይ በሚመለከት ከፓርቲው የተለየ አቋም መያዛቸውን በይፋ አሳወቁ። ኮ/ል ጎሹ የግል አስተያየቴ ነው በሚል ስለ ኤርትራ ሲናገሩ፤-

> *" ... የዛሬ አስር ዓመት ኤርትራ በወያኔ ግምባር ቀደም አጋፋሪነት ተገንጥላ ዛሬ ይኸውና የመላው ዓለም መንግስታት እውቅና አግኝታ የተባበሩት መንግስታትም ጭምር በዓለም አቀፍ የፖለቲካ ስርዓትም ውስጥ ታቅፋ በዓለም ህግም ተጠብቃ ነፃ አገር ሆና ትኖራለች። እርግጥ በዚያ ረጅም ጦርነት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ጀግኖች ኢትያጵያውያን በምድረ ኤርትራ ወድቀው ቀርተዋል። የእኔም የቅርብ ጓደኞች መኮንኖች ጭምር። የብዙ እናቶችና አባቶችም አንጀት ጭመር እርር ብሏል። በመሆኑም ለብዙ ኢትዮጵያውያን ዜጎችና ድርጅቶች የኤርትራ መገንጠል ለምን ሊዋጥ እንዳልተቻለ ይገባኛል። እህቶቼና ወንድሞቼ አብሮ ለመኖር ቢቻል ጥሩ ነበር። ነገር ግን አልተቻለም። ይሄ ነው። ሐቁ የሄ ነው። ታዲያ መልካም እድል ያጋጥማችሁ ብሎ መሰነባበት እንጂ ምን ለማድረግ ይቻላል። ከእንግዲህ ወዲህ ወደኋላ ተመልሰን ታሪካዊ ቁስላችንን በማስታመም ፋንታ ያንን ምዕራፍ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዘግተን ወደፊት መጓዝ ይኖርብናል። በእዚህ አገር አነጋገር ' Move on' የላሉ። የእንግሊዘኛ ቃል በመጠቀሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ... "*

ኮ/ል ጎሹ ወልዴ
በዋሽንግተን ዲሲ በተደረግ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ካደረጉት ንግግር የተወሰደ
ጁን 17 ቀን 2001 ዓ.ም

ይህ የኮ/ል ጎሹ ወልዴ አቋም መድኅን በኤርትራ ጉዳይ ላይ ካለው አቋም ጋር ፈጽሞ የሚጻረር በመሆኑ ንግግሩን ያዳመጡ የድርጅቱ አባላትንና ደጋፊዎችን በሙሉ አስደነገጠ። ዛሬ እሳቸው እንደሚሉት ከመድኅን ጋር ያላቸው ልዩነት የስልት ብቻ ሳይሆን የዓላማም ጭምር መሆኑን ይህ ንግግራቸውና አቋሚቸው በግልጽ ያሳየናል። ኮ/ል ጎሹ መድኅን በኤርትራ ላይ ያለውን አቋም ላለመቀበል ምክንያት የሆናቸውን ጉዳይ ለማወቅ ባይቻልም አንድ ግለሰብ ትናንት ይከተል የነበረውን አቋም ዛሬ ሲለውጥ ማየቱ የነበረና ያለ በመሆኑ አዲስ ላይሆንብን ይችላል። ሆኖም ግን እንዲህ ዓይነቱ ድንገተኛ ሥር ነቀል የአቋም ለውጥ እንኳን እንደ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ መድኅንን ከምስረታው ጀምሮ ለአራት ዓመታት ከመራና በኤርትራ ጉዳይ ላይ የመድኅንን አቋም በመወከል ሽንጡን ገትሮ ከተባበሩት መንግስታት ማህበር ጋር ከታገለ የፓርቲው ባለስልጣን ይቅርና ከአንድ

ተራ አባል የሚጠበቅ አልነበረም። እንዲህ ዓይነቱ ከድርጅቱ ፕሮግራም ውጭ የሆነ አቋም በግል አስተያየት ሽፋን እንደ ቀልድ ወርወር ሲደርግ በወቅቱ በቀላሉ መታለፍ አልነበረበትም።

እንደገና አሁን በቅርቡ ከሁለት ዓመት በኋላ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ወደ ድሮው አቋማቸው መመለሳቸውን የሚያሳይ ዜና ዘፕሬስ ጋዜጣ ላይ አንቢቢያለሁ። ጋዜጣው *"በሁለት ወገን ሰላማዊ ሰልፍ ሊካሄድ ነው"* በሚል ርዕስ ሥር ባቀረበው ዜና በአንድ በኩል በቅርቡ በተመሰረተው የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ኀብረት (ኢዴኃህ) በሌላ በኩል ደግሞ በእነ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ሊካሄድ ስለታሰበው የተቃውሞ ሠልፍ ሲዘግብ፡-

> *" … በህብረቱ ምስረታ ጉባዔ ያልተሳተፉና የህብረቱ አባል ያልሆኑት እነ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ፣ ንጉሴ ወልደ ማርያም፣ መ/አ ምርጫውና ሌሎች ወገኖች በሔግ ተሰይሞ የነበረውን የድንበር ገላጋይ ኮሚሽን የሰጠውን ውሳኔ በተለይም የባድሜን ወደ ኤርትራ ግዛት ውስጥ መካለል በመቃወም በቅርብ ቀን ውስጥ ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄድ ጥሪ በማስተላለፍ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን … "*

ዘፕሬስ ነሐሴ 21 ቀን 1995 ዓ.ም

ኢዴኃኅ በኦክቶበር 3 ቀን 2003 ዓ.ም ታላቅ የተቃውሞ ሠልፍ በዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ያካሄድ ሲሆን ኮ/ል ጎሹ ወልዴም ወደ ሶስት ከሚሆኑ በዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ከሚገኙ የሬዲዮ ጣቢያዎች ጋር በመተባበር የኢትዮጵያ ድንበር ቀይ ባህር መሆኑንና የሔጉን ውሳኔ በመቃወም በአኦክቶበር 6 ቀን 2003 ዓ.ም የተቃውሞ ሠልፍ አካሂደዋል። እንደ ኮ/ሉ መግለጫ ከሆነ በኢዴኃኅ ሠልፍ ላይ ወደ ሁለት መቶ ሃምሳ ኢትዮጵያዊያኖች የተገኙ ሲሆን እሳቸው በጠሩት በኦክቶበር 6 ቀን ሠልፍ ላይ ግን ከዘጠኝ መቶ የማያንሱ ሠልፈኞች እንደተገኙ ነግረውናል። ሆኖም ግን የሠልፉ አስተባባሪ የሆኑትና በኮ/ል ጎሹ ወልዴ የመድኅን አንጃ ቡድን ውስጥ ንቁ አባል የሆነቱ መቶ አለቃ ምርጫው ቪኦኤ (VOA)የህብረቱን ሠልፍ በተመለከተ በምሽት ፕሮግራሙ ላይ ሲዘግብ የኮ/ል ጎሹን ሠልፍ ግን ቪኦኤ አለመዘገቡ እንዳሳዘናቸው ራሳቸው መ/አለቃ ምርጫው በሚቆጣጠሩት የኢትዮጵያዊነት ሬዲዮ ላይ ገልጸዋል።

… ይቀጥላል